የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ባለሥልጣን
ETHIOPIAN CAPITAL MARKET AUTHORITY

**February 05, 2026**
Ethiopian Capital Market Authority
Addis Ababa, Ethiopia

# TO: SHARE COMPANIES THAT HAVE NOT YET REGISTERED THEIR SHARES

As is well known, Article 29 of the Public Offering and Trading of Securities Directive No. 1030/2024 stipulates that securities held by the public prior to the issuance of the directive must be registered with the Ethiopian Capital Market Authority (ECMA). Accordingly, the deadline provided by the Directive for the registration of existing securities expired on November 25, 2025.

However, we have noted that while many companies have registered their securities or submitted their registration statements within the legally prescribed deadline, there remains a significant number of companies that have not yet submitted their registration applications.

Therefore, the Authority strictly urges share companies that have a mandatory obligation to register existing shares but have not yet done so to understand that remaining unregistered will have a negative impact on the administrative measures taken against the company. You are required to complete the registration by providing the necessary documentation and an explanation for the failure to register within the original deadline.

---

**For enquiries & additional information contact**

**Contact:** Communications & Public Relations Directorate
**Phone:** 011-5-57-81-62
**Email:** communication@ecma.gov.et

ጥር 28፣ 2018 ዓ.ም
የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ባለስልጣን
አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

# አክስዮናችሁን ያላስመዝገባችሁ አክስዮን ማህበራትን ይመለከታል

እንደሚታወቀው በሰነደ ሙአለ ንዋይን ለህዝብ የማቅረብ እና ግብይት መመሪያ ቁጥር 1030/2017 አንቀጽ 29 ላይ መመሪያው ከመውጣቱ በፊት በህዝብ የተያዙ ሰነደ ሙአለ ንዋዮች በኢትዮጵያ ካፒታል ገበያ ባለስልጣን መመዝገብ ያለባቸው መሆኑ ተደንግጎ ይገኛል፡፡ በዚህም መሰረት ነባር ሰነደ ሙአለ ንዋዮችን ለማስመዝገብ በመመሪያው የተሰጠው ቀነ ገደብ ህዳር 16 ቀን 2018 ዓ.ም ተጠናቋል፡፡

በርካታ ኩባንያዎች ሰነደ መዋለ ንዋያቸውን በህጉ በተቀመጠው ቀነ ገደብ ያስመዘገቡ አሊያም የምዝገባ መግለጫቸውን ያስገቡ ቢሆንም እስካሁን የምዝገባ መግለጫ ያላስገቡ ቁጥራቸው በርከት ያለ ኩባንያዎች መኖራቸውን ተገንዝበናል፡፡ በመሆኑም አሁንም የማስመዝገብ ግዴታ እያለባችሁ ነባር አክስዮኖችን ያላስመዘገባችሁ አክስዮን ማህበራት ሳታስመዘግቡ የምትቆዩበት ጊዜ በኩባንያው ላይ የሚወሰደው አስተዳደራዊ እርምጃ ላይ አሉታዊ ውጤት የሚኖረው መሆኑን ተገንዝባችሁ ተገቢውን ማስረጃዎች በማሟላት እና በጊዜ ገደቡ ምዝገባውን ያላከናወናችሁበትን ምክንያት ከመግለጽ ጋር ምዝገባውን እንድታከናውኑ ባለስልጣኑ በጥብቅ ያሳስባል፡፡

**ለጥያቄዎችና ተጨማሪ መረጃ**
**የኮሙኒኬሽን እና የህዝብ ግንኙነት ዳይሬክቶሬት**
**ስልክ:** 011-5-57-81-62
**ኢሜይል:** communication@ecma.gov.et